# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 23 ኛ ሳምንት

## ወዳጆቹ የረዱት በሽተኛ

**ዓላማ**

- እርሱ በርሳችን እንድንተዛዘንና መረዳት ያለባቸውን ሰዎች ስለመርዳት መማር፡፡

**መግቢያ**

- ማርቆስ 2፥1-12

**መግቢያ**

- ይህ የእምነትና ወዳጅነትን ኃይል የያዘ ታሪክ ነው፡፡
- በዚህ ትምህርታችንም ሽባ የነበረ ጓደኛቸውን ወዳጆቹ ለመርዳት ምን ያህል እንደጣሩ እንማራለን፡፡
- በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የነበራቸውንም ጠንካራ እምነት እናያለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ሚስትና ልጆች ያልነበሩት አንድ ሽባ ሰው ነበረ፡፡የሚረዱትና እንዲድን የሚጥሩለት አራት ወዳጆችም ነበሩት፡፡
- አንድ ቀንም ጌታችን በከተማ ውስጥ እንዳለ ሰምተው፡፡ጓደኛቸውን ተሸክመውም ወደ ክርስቶስ ወሰዱት፡፡
- ጌታችን ከነበረበት ቤት ሲደርሱም፥ትምህርቱን የሚማሩ ብዙ ሰዎች ነበሩና መግባት አልቻሉም
- ወደጃቸውን ወደ ክርስቶስ ለማቅረብ ወስነው ነበርና፡፡ወደ ቤቱ ጣራ ወጥተው ጣራውን ከከፈቱ በኂላ ሽባውን ከተኛበት አልጋ ጋር ወደ ቤቱ አወረዱት፡፡
- ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነታቸው ተደንቆ ***"አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ተነሣ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ"*** አለው፡፡ ወዲውም ተነሥቶ፣ አልጋውን፣ ተሸክሞ፣ በሁሉም ፊት ሄደ፡፡
- በቤቱም የነበሩ ሰዎች ሁሉም ተገሩሙና እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ፤አመሰገኑም፡፡

**ደብረዘይት**

ልጆች ከነገ ጀምሮ ያለው ሳምንት በቤተክርስቲያን ደብረዘይት /እኩለ ጾምም/ይባላል፡፡

- ደብረዘይት ማለት ምን ማለት ነው?
  - ✓ የዘይት ተራራ ማለት ነው፡፡
- ለምን እንዲህ ተባለ?
  - ✓ ዘይት የሚወጣ የወይራ ዛፍ በብዛት ያለው ተራራ ስለሆነ ደብረ ዘይት ተብሎል
- ታዲያ እኛ ለምን ደብረዘይትን እናከብራለን?
  - ✓ ጌታችን በዚህ ተራራ ስላስተማረ፡፡
- ምን አስተማረ?
  - ✓ ስለዓለም መጨረሻና ደግሞ ምጽአቱ፡፡
- እኩለ ጾም ማለት ምን ማለት ነው?
  - ✓ የጾም አጋማሽ ማለት ነው፡፡
- ለምን እንዲህ ተባለ?
  - ✓ ከዐቢይ ጾም ሳምንታት የመካከለኛው ሳምንት ስለሆነ፡፡
  - ✓

**መዝሙር**

ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መሥክሩ
ተዓምሩን ለዓለም ንገሩ (2) ድንቅ ሥራውን መስክሩ

**ጥያቄ**

1. ሽባ የነበረውን ሰው እንዴት
2. ጌታችን ምን ብሎ አደነው?
3. ከዚህ ምን ተማራችሁ?

**ተግባር**

- ሁሌም በእግዚአብሔር ፍጹም እምነት ይኑራችሁ፡፡
- በመሰናክሎች ተስፋ አትቁረጡ
- አስተዋዮችና ዘዴኞችም ሁኑ፡፡
- ለወዳጆቻችሁና በተለይም የተጎዱ ሰዎችን ተባበሩ፡፡

**ይቆየን፡፡**